MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

# የተጠረጠረ በደል እና የቸልተኝነት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

Office of District Operations
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850

MCPS ቅጽ 335-44
ኦገስት 2022

*መመሪያዎች፡-* የቃል ሪፖርትወዲያውኑ "Child Welfare Services, Montgomery County Department of Health and Human Services (DHHS)" (የልጅ (ጥቃት/በደል) መከላከያ አገልግሎት/ Child Protective Services/ (CPS) ተብሎ ለሚታወቀው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰው ሃይል አገልግሎት መምሪያ (DHHS) የልጆች ጥበቃ ተራድኦ አገለግሎት 240-777-4417 በመደወል ሪፖርት መደረግ አለበት። ለጥቃት/ለጉዳት የተጋለጡ/አቅመ ደካማ አዋቂ ሰዎችን በተመለከተ፣ ለትልቅ ሰው (ጥቃት/በደል) መከላከያ አገልግሎቶች/Adult Protective Services (APS) በ240-777-3000 ላይ ይደውሉ። ይህ አደጋ/አስቸኳይ ከሆነ ወዲያውኑ ወደ 911 ይደውሉ። ከጾታዊ ጥቃት ጋር በተያያዘ ለሚጠረጠር ጥቃት ወይም ቸልተኝነት፣ የአደጋ ጊዜ የግንኙነት ማዕከል "Emergency Communications Center (ECC)" 240-683-1600 ይደውሉ። ይህን የጽሁፍ ሪፖርት ሞልተው 48 ሰዓታት ውስጥ ያቅርቡ።

የበደል እና ቸልተኝነት ሁኔታን ሪፖርት በማድረግ እና ባለማድረግ ላይ ጥርጣሬ የሚኖር ከሆነ፣ ሁልጊዜ ቢሳሳቱም እንኳ ሪፖርት ማድረጉን ይምረጡ።

MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች ማንኛውምን ተጠርጣሪ ተጎጂ፣ ምስክር፣ ወይም ጥቃት አድራሽ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ወይም ከእነርሱ የጽሁፍ መግለጫዎችን መሰብሰብ አይኖርባቸውም።

## ክፍል I — የቃል እና የጽሁፍ ሪፖርት በሚያደርገው/በምታደርገው ግለሰብ የሚሞላ

ስም______________________ ኃላፊነት ______________________

የትምህርት ቤት ስም ______________________ ኢሜል፡-______________________

የት/ቤት አድራሻ ______________________ የት/ቤት ስልክ _____-_____-______
መንገድ ከተማ ስቴት ዚፕ

## ክፍል II—ስለ ልጅ ወይም አቅመ ደካማ አዋቂ ሰው መረጃ (በሪፖርት አድራጊው/ዋ የሚታወቅ/የምትታወቅ ከሆነ/ች)

አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ምልክት ያድርጉ:- (የሚመለከተውን ሁሉ ምልክት ያድርጉ) ❑ ማጎሳቆል (ይግለጹ፡ አካላዊ እና/ወይም ❑ ወሲባዊ ጥቃት) ❑ ቸልተኝነት ❑ የአእምሮ ጉዳት

የልጁ (የልጅቱ) የልደት ቀን ___/_____/_____ ዕድሜ______

ወሲባዊ ጥቃት ከተጠረጠረ፣ ርእሰመምህር/ሱፐርቫይዘር ለአደጋ ጊዜ የግንኙነት ማዕከል "Emergency Communications Center (ECC)"፣ MCPD፣ ወዲያውኑ 240-683-1600 መደወል አለባቸው።

የልጅ ስም ______________________ ጾታ፡ ❑ ሴ ❑ ወ_______የዘር ሐረግ ክፍል___

አድራሻ ______________________

ወንድሞች እህቶች (ከታወቁ) ______________ ____ ____ ______________ ____ ______________
ሥም እድሜየሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት ሥም እድሜ የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት

ወንድም እህቶች (ከታወቁ) ______________ ____ ______________ ______________ ____ ______________
ሥም እድሜየሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት ሥም እድሜ የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት

## ክፍል III—ለልጁ/ልጅቷ ወይም ለአቅመ ደካማው/ዋ ትልቅ ሰው እንክብካቤ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት/ባት ግለሰብ (በሪፖርት አድራጊው/ዋ የሚታወቅ/የምትታወቅ ከሆነ)

| | |
|---|---|
| በአሁኑ አድራሻ ለሚኖር ልጅ ኃላፊነት ያለው የአዋቂ ስም፡-<br>______________________ | በአሁኑ አድራሻ ለሚኖር ልጅ ኃላፊነት ያለው የአዋቂ ስም፡-<br>______________________ |
| ዝምድና (ግንኙነት)፡- ❑ እናት ❑ አባት ❑ ሞግዚት | ዝምድና (ግንኙነት)፡- ❑ እናት ❑ አባት ❑ ሞግዚት |
| ሌላ ______________________ | ሌላ ______________________ |
| ስልክ #1 _____-_____-______ ስልክ #2_____-_____-______ | ስልክ #1 _____-_____-______ ስልክ #2_____-_____-______ |
| ስልክ ቁጥር #3 _____-_____-______ | ስልክ ቁጥር #3 _____-_____-______ |

## ክፍል IV—የጉዳቱን ወይም የአስጊ ሁኔታውን ባህሪ (መግለጽ አስፈላጊ ቢሆንም:- የተጠረጠረውን በደል/ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ትክክለኛነት ለመወሰን ምርመራ ማድረግ የማንም MCPS ሠራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ኃላፊነት አይደለም)። MCPS ቅጽ 336-01 ይጠቀሙ፡- MCPS ቅጾች እንደተጨማሪ ሆኖ የሚያገለግል፣ አስፈላጊ ከሆነ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ ፖሊሲ JHC እና MCPS መመሪያ JHC-RA ይመልከቱ።

እባክዎ የሚያሳስብዎትን ምክንያቶች ይግለጹ እና ልጁ/ልጅቱ ወይም ተጎጂው ጎልማሳ የተጎጅነት ወይም የቸልተኝነት ሰለባ ሊሆን ይችላል/ልትሆን ትችላለች የሚል ጥርጣሬ እንዲፈጠር ምክንያት የሆነውን ሁኔታ እንዴት እንዳወቁ ይግለጹ። አሁን የተፈጠሩትን ጉዳቶች አግባብ ከሆነ፣ መረጃ ያካቱ።

በዚህ/ች ልጅ ወይም አቅመ ደካማ አዋቂ ሰው ወይም በሌሎች በዚህ ቤተሰብ ሁኔታ ውስጥ፣ ስለደረሱ/ስለነበሩ ቀደም ያሉ CPS ወይም APS ተሳትፎን ጨምሮ፣ በደል/ጥቃት ወይም የቸልተኝነት ጉዳቶች ወይም ሁኔታዎች መረጃ ይስጡ፡-

## ክፍል V— ከታች የተጠየቀውን መረጃ ይሙሉ

የቃል ሪፖርት የተደረገበት ቀን _____/_____/______ የቃል ሪፖርት የተደረገበት ሠዓት _____፡_____ ጠዋት/ከሰዓት (a.m./p.m.)

የቃል ሪፖርት የተደረገለት/ላት CPS ወይም APS ሠራተኛ አባል ሥም (እባክዎን ይጻፉ)______________________

ርእሰ መምህሩ/ሯ/ተቆጣጣሪው/ዋ እንዲያውቁት የተደረገበት ቀን እና ሰአት ቀን _____/_____/______ ሠዓት___:___ ጠዋት/ከሰዓት (a.m./p.m.)

ይህ ቅጽ ወደ CPS የተላከበት ቀን ወይም APS _____/_____/_______ ሪፖርት የሰጠው ሰው ፊርማ ______________________

ስርጭት፡-
ቅጅ 1፡- CPS ፤ DHHS, 1301 Piccard Drive, Rockville, MD 20850, ስልክ :- 240-777-4417፤ ወይም APS፣ DHHS, 401 Hungerford Drive፣ 3rd Floor, Rockville, MD 20850 ፤ ስልክ :- 240-777-3000
ቅጅ 2፡- MCPS Systemwide Child Abuse Contact, Office of District Operations, CESC, Room 55, Phone: 240-740-3215
ቅጅ 3፡- Office of the State's Attorney for Montgomery County, County Office Building, 50 Maryland Avenue, 5th Floor, Rockville, MD 20850;
ቅጅ 4፡- Special Victims Investigations Division, Montgomery County Police Department, 7300 Calhoun Place, Suite 300, Rockville, MD 20855.

ምስጢራዊ መረጃ የያዙ የተጠረጠረ በደል እና ቸልተኝነት ሪፖርቶች ካልተፈቀደ በቀር ሊሰራጩ ፣ ሊበተኑ ፣ ወይም ሊገለበጡ/ኮፒ ሊደረጉ አይችሉም። መግለጽ፣ ኮፒ ማድረግ፣ ማሰራጨት፣ ወይም በዚህ መረጃ ይዘት ላይ መሰረት በማድረግ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድ በጥብቅ የተከለከለ ነው።

የበደል እና ቸልተኝነት ሁኔታን ሪፖርት በማድረግ እና ባለማድረግ ላይ ጥርጣሬ የሚኖርዎት ከሆነ፣ ቢሳሳቱም እንኳ ሁልጊዜ ሪፖርት ማድረጉን ይምረጡ።

## ትርጉም

በደል (ጥቃት) ማለት፡-

1. ማንኛውም የአካል መጎዳት በግልጽ የማይታይም ቢሆን፣ አእምሮው የተጎዳ ልጅ ወይም ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት ጠባቂ/ተንከባካቢ ወይም ክትትል በሚያደርግ ሰው አማካይነት የተፈጸመ፣ የልጁ/የልጅቱን ወይም ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰውን ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት በሚዳረግ/በሚያጋልጥ ሁኔታ ወይም የተ ጎዳ/ች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ።
2. ማንኛውም የወሲባዊ ድርጊት ወይም ድርጊቶች (ለአካላዊ ጉዳቶች ይዳርጉ ወይም አይዳርጉ) እንደ የልጆች ወሲባዊ በደል/ጥቃት ወይም ብዝበዛ፣ በዘመዳማቾች መካከል የሚደረግ የወሲባዊ ግኑኝነት፣ መድፈርን፣ በማንኛውም ደረጃ ወሲባዊ ጥቃት መፈጸምን፣ ግብረሶዶማዊ ወይም ተፈጥሯዊ ያልሆነ ወይም ያልተለመደ እና ተቀባይነት የሌለው የወሲብ ልምም ዶችን ያካተተ በልጅ ወይም በአቅመ ደካማ ትልቅ ሰው ላይ፣ ቋሚ ወይም ጊዚያዊ የማሳደግ ወይም ልጁ/ጅቷን ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ሰው የመንከባከብ ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት ባለበ/ባት በማንኛውም ሰው የደረሰ/የተፈጸመ። ያታዊ ትንኮሳ ወይም ማጎሳቆል የሚያካትተው፣ በዚህ አይወሰንም፣ ትንሽ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ራቁት ሰውነት መነካካት፣ ብልት በማሳየት ለግብረስጋ ማነሣሣት፣ ሩካቤ ስጋ ማድረግ/ማስገባት፣ መሳም፣ መደባበስ/ማሻሸት፣ በማንኛውም ደረጃ ጾታዊ ወንጀል መፈጸም፣ አስገድዶ መድፈር፣ ወራዳነት፣ ሸርሙጥና፣ በህገወጥነት ሰዎችን ማዘዋወር፣ ወይም መፍቀድ/ፈቃድ መስጠት፣ ማደፋፈር፣ ወይም ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ወሲብ ቀስቃሽ ምስል/ፅሁፍ ማሳየት፣ ፎተግራፍ ማንሣት፣ ፊልም መቅረጽ፣ ወይም ስለ ትንሽ ልጅ ወይም ደካማ ትልቅ ሰው በህግ የተከለከለ የጽሑፍ/ሥዕላዊ ገለጻ፣ ወይም ትንሽ ልጅ ወይም አቅመደካማ ትልቅ ሰውን አስገድዶ የመድፈር ወንጀል በመሥራት የተመዘገበ ሰው ባለበት ወይም ሁልጊዜ በሚገኝበት አካባቢ እንዲቆዩ/እንዲኖሩ መፍቀድ።

ልጅየሚመለከተው ማንኛውም MCPS ተማሪ፣ የተማሪው(ዋ) እድሜ ምንም ይሁን ምን፣ እና ሌላ እድሜው/ዋ 18 አመት በታች የሆነ(ች) ማንኛውም ሰው ነው። ምንም እንኳን የሜ ሪላንድ ህግ 18 አመት በላይ የሆነ/ችን ተማሪ በደል ወይም ቸልተኝነትን በአጠቃላይ እንደ ወንጀል ባይወስደውም፣ MCPS ይህን የመሰለ ሁኔታ 18 አመት በታች በሆነ(ች) ልጅ ላይ ደርሷል ተብሎ የተጠረጠረን በደል እና ቸልተንነት ሪፖርት የሚደረግበትን ተመሳሳይ አካሄዶች በመጠቀም ሪፖርት እንዲደረግ ይጠብቃል።

የአእምሮ ጉዳትማለት ለልጁ/ጅቷ ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ትልቅ ሰው ዘላቂ ወይም ጊዜያዊ የማሳደግ/የመጠበቅ ወይም ልጁ/ጅቷን ወይም አቅመ ደካማው/ዋን ትልቅ ሰው ለመን ከባከብ ወይም ለመቆጣጠር ኃላፊነት ባለበት በማንኛውም ሰው ድርጊት ምክንያት ሊታይ የሚችል፣ እና የልጁ/ጅቷ ወይም የአቅመ ደካማው/ዋ ትልቅ ሰው አእምሮ ወይም የስነ-ልቦና ችሎታ በአግባቡ ለመስራት በጉልህ መጎዳት/መጉደል ነው።

ችላ ማለት ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ብቻው(ዋ)ን መተው ወይም ሌላ ተገቢ እንክብካቤ ያለማድረግ፣ ወይም ትኩረት አለመስጠት፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ አያያዝ ወይም ትኩረት መንፈግ፣ ልጅ ወይም ደካማ ለጉዳት የተጋለጠ አዋቂ ሰው በማንኛውም ወላጅ፣ ጠባቂ፣ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የ MCPS ሠራተኛ፣ በጎ ፈቃደኛ፣ ወይም ኮንትራ ክተር፣ ኃላፊነትው ያለው/ያላት ሰው፣ ወይም ማንኛውም በጊዜያዊነት ወይም በመደበኛነት የሚጠብቅ ሰው፣ ስለህፃኑ ወይም ደካማ ጎልማሳ ሰው ያሉበት አስጊ ሁኔታ የመቆጣጠር ኃላ ፊነት ያለበት ሰው የሚከተሉትን አመላካች የሆነ —

ሀ) የልጅ ወይም አቅመ ደካማ አዋቂ ሰው ጤና ወይም ደህንነት ሲጎዳ ወይም በሚታይ/ጉልህ የመጎዳት አደጋ ላይ ሲሆን፣ ወይም
ለ) በልጅ ወይም አቅመ ደካማ አዋቂ/ትልቅ ሰው ላይ የአእምሮ ጉዳት ሲደርስ ወይም ሊደርስ ያለ የአእምሮ ጉዳት ጉልህ አደጋ።

ለችግር የተጋለጠ ጎልማሳ ሰውማለት፡- 18 ዓመት እድሜ ወይም የበለጠ ሪፖርት በሚያደርገው/በምታደርገው ግለሰብ የተጎሳቀለ ወይም ችላ የተባለው የእለት ተእለት ፍላጎትን ለመንከባ ከብ አካላዊ ወይም የአእምሮ ብቃት እንደሌለው ሲታመን ነው።

## ሪፖርት ማቅረቢያ/ማድረጊያ መስፈርቶች

1. ሁሉም MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭዎች ማንኛውንም የሚጠረጠር የልጅ በደል ወይም ቸል መባል አጋጣሚ በግል እና በቀጥታ እን ዲያመለክቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲ ነው።
   - ተጠቂ ነው/ናት ተብሎ/ላ የሚጠረጠረው/የምትጠረጠረው በአመልካቹ/ቿ በግለሰብ ደረጃ ይታወቅም/ትታወቅም አይታወቅም/አትታወቅም።
   - ድሮ በደል እንደደረሰ ለማመን ምክንያት በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ፣ ምንም እንኳን አጋጣሚው ሲታወቅ/ሲገለጥ ተጠርጣሪው/ዋ ተጎጂ ትልቅ ሰው ቢሆንም/ብትሆንም።
   - ልጁ/ልጂቱ ወይም አቅመ ደካማው/ዋ አዋቂ የትም ይኑር/ትኑር እናም የተጠረጠረው በደል ወይም ቸል መባል /ተገቢውን እንክብካቤ ያለማግኘት ተፈፀመበት የተባለው ስፍራ የትም ይሁን የት።
2. የተጠረጠረን በደል ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ አሳማኝነቱን ለመወሰን መመርመር የማንም MCPS ሠራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ኃላፊነት አይደለም።
3. ስለተጠረጠረ የልጅ በደል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚቀርብ የቃል ሪፖርት ወዲያውኑ መቀረብ አለበት።

**የልጅ መበደልን ፣ ቸልተኝነትን፣ እና የአእምሮ ጉዳት ሪፖርት ለማድረግ የሚከተለውን ቁጥር ይደውሉ፡- 240-777-4417**
**የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎቶች**
Child Protective Services, Department of Health and Human Services (24 hours)

**ስለአቅመ ደካማ አዋቂ ሰው በደል ወይም ቸልተኝነት ሪፖርት ለማድረግ በሚከተለው የስልክ ቁጥር ይደውሉ፡- 240-777-3000**
**የአዋቂ ሰዎች የደህንነት ጥበቃ የጤና እና የሰው ኃይል አገልግሎቶች መምሪያ**
Adult Protective Services, Department of Health and Human Services

**የወሲብ ጥቃት ከተጠረጠረ ርእሰመምህር፣ ሱፐርቫይዘር በዚህ የስልክ ቁጥር ይደውላል/ትደውላለች፡- 240-683-1600**
Emergency Communications Center, Montgomery County Police Department
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት የአደጋ ጊዜ ግንኙነት ማእከል**

4. የጽሁፍ ሪፖርት CPS ወይም APS፣ የጤና እና የሰው ኃይል አገልግሎቶች መምሪያ 48 ሰአታት ውስጥ መቅረብ አለበት። MCPS ቅጽ 335-44 ፣ የተጠረጠረን በደል እና ቸልታ ሪፖርት ለማድረግ (Report of Suspected Abuse and Neglect) ይጠቀሙ። አድራሻ እና የስርጭት ሁኔታ በቅጹ ላይ ተገልጿል ። ይህን መመሪያ በተመለከተ ምንም የተለየ አስተያየት አይደረግም።
5. ሁሉም ሪፖርቶች በልሙጥ ፖስታ ታሽገው እና አድራሻ ተጽፎባቸው ምስጢራዊ የሚል ምልክት ተደርጎባቸው መላክ ይኖርባቸዋል ። ለ "Office of School Support and Improvement" ጽ/ቤት የተላኩ ሪፖርቶችን የያዙ ፖስታዎች በተለመደው አይነት ከጽ/ቤት ወደ ጽ/ቤት መላኪያ ፓስታ መደረግ ይኖርባቸዋል።
6. በሜሪላንድ ህግ ማንም ሰው በቀና መንፈስ በደል ወይም ቸልተኛነት ሪፖርት ካደረገ/ች ወይም ሪፖርት በማድረግ ከተሳተፈ/ች ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በሚመጣ የፍርድ ሂደት ከተሳተፈ(ች) በሌላ ሁኔታ የበደልን ወይም ቸልተኝነትን፣ ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በመጣ የፍርድ ሂደት በመሳተፍ ሊመጣ ከሚችል ሲቭል (የፍትሃብሄር) ተጠያቂነት ወይም ከወንጀል ቅጣት ነጻ ይሆናል/ትሆናለች።
7. ማንኛውም MCPS ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ወይም የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች፣ MCPS በሙያ ወይም አገልግሎት በመስጠት የስራ ድርሻቸው ላይ በተገኙበት ሁኔታ፣ የልጅ በደል እና/ወይም ቸልተኝነትን ጠርጥረው እያውቁ ጉዳዩን ሪፖርት ካላደረጉ፣ ወይም ሆን ብለው ሪፖርት እንዳይደረግ ከከለከሉ ወይም ጣልቃ ከገቡ፣ የማይገባ ጠባይ በማሳዬት እንደ አግባብነቱ ከስራ እስከመታገድ፣ የኮንትራት አገልግሎቶቻቸው እስከመቋረጥ፣ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመስጠት እድላቸው እስከመቋረጥ የሚያደርስ የስነ ስርአት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። በተጨማሪ ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ወይም በሌላ የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰጭ ቦርድ ሥልጣን የተሰጠ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ፣ በሜሪላንድ ህግ በተቀመጠው መስፈረት መሰረት ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ ፖሊሲ JHC እና MCPS ደንብ JHC-RA ይመልከቱ።

ምስጢራዊ መረጃ የያዙ የተጠረጠረ የበደል እና ቸልተኝነት ሪፖርቶች ካልተፈቀደ በቀር ሊሰራጩ፣ ወይም ኮፒ ሊደረጉ አይችሉም።
መግለጽ፣ ኮፒ ማድረግ፣ ማሰራጨት፣ ወይም በዚህ መረጃ ይዘት ላይ ተንተርሶ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድ በጥብቅ የተከለከለ ነው።